# የቅዱስ ሲኖዶስን ስምና ሥልጣን የተጠቀመው የመናፍቃኑ መግለጫ!

ቅዱስ ሲኖዶስ ያደረገውን ዓመታዊ ስብሰባው በቀደም ጥቅምት 26 2008 ዓ.ም. ሲቋጭ ጠንከር ያለ ባለ ዘጠኝ ነጥብ የሦስት ገጽ መግለጫ አውጥቶ ነበር፡፡ መግለጫው በሀገራችንና በሕዝቧ ላይ ወያኔ እያደረሰው ያለውን ጥፋት በማውገዝ ሀገራችን ለገጠማት ችግር ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ሲኖዶሱ ይሄንን ማድረጉ ከማንም በላይ የሚመለከተው ጉዳይ በመሆኑ የሚያስመሰግነውና ማድረግም ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ሲኖዶስ ብየ ስል በስደት አሜሪካ ያለውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤን ወይም አሥተዳደርን ማለቴ ነው፡፡ እርግጥ ነው እዚህ ሀገር ቤት አራት ኪሎ የሚገኙት እግዚአብሔርን ሳይፈሩና ሳያፍሩ እረኝነታቸው ሳይቆጫቸው ወያኔ በልጠባቸው ያላቸውን አቅም አሚጠው ወያኔን በትጋት እያገለገሉ ያሉ "ጳጳሳት" እና ወያኔን ማገልገል ባይፈልጉም ወያኔን ከሚያገለግሉት ጋር ከማጫፈር ያለፈ ሌላ ሚና መጫወት ያልቻሉት የወያኔ መጫወቻ መቀለጃ የሆኑት የተቀሩት ጳጳሳትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ እኛ ነን ይላሉ፡፡ ይሁንና የቤተክርስቲያን ሕግና ቀኖና የሚቀበለውና የሚያውቀው የቤተክርስቲያኗ ሲኖዶስ ግን በስደት ያለው ሲኖዶስ እንጅ በወያኔ ወሳኝነት እራሳቸውን ፓትርያርክ አድርገው የሾሙትና ሲኖዶስ ነን የሚሉትን የጳጳሳት ቡድን አይደለም፡፡

ሲኖዶስ ይሰደዳል ወይ? ምንትስ ለሚሉ ጥያቄዎች ከዚህ ቀደም መጽሔቶች ላይ በጻፍኳቸው ጽሑፎች መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ከሌሎች የቤተክርስቲያኗ የሕግ የሥርዓትና የቀኖና መጻሕፍት ድንጋጌዎችና አስተምህሮዎች አንጻር በስፋት የዳሰስኩት ጉዳይ ስለሆነ አሁን እዚህ ላይ አልመለስበትም፡፡

ቅዱስ ሲኖዶሱ ሌላው ትኩረት የሰጠውና በመግለጫው ላይ በቅድሚያ ያነሣው ጉዳይ ደግሞ ቅድስት ቤተክርስቲያን የመንጋዋን በአስደንጋጭ ሁኔታ መቀነስ በተመለከተ አባ ማትያስ የተናገሩትን በመጥቀስ ለዚህ የቤተክርስቲያን ጉዳትና ኪሳራ ተጠያቂው ወያኔ ነው በማለት ወያኔ እንዴት አድርጎ ምእመናን እንዲቀንሱ እንዳደረገ አምስት ነጥቦችን ጠቅሷል፡፡

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ በሲኖዶስ ውስጥ እንዳሉ የሚታወቁት መናፍቃን ጳጳሳትና ካህናት የጥፋት ሥራቸውና ሸረኛ ተግባራቸው እጅግ አሳፋሪ በሆነና "ምን ይሉናል!" የሚል ቅንጣት ሥጋት ባልታየባቸው መልኩ ድፍረትና ንቀት የተሞላበት ነውረኛ ተግባራቸው ቁልጭ ብሎ የታየው፡፡

እነኝህ የሲኖዶስ አባላት መናፍቃን ጳጳሳት ቤተክርስቲያን የመንጋዋ በአስደንጋጭ ሁኔታ የቀነሰበትን ትክክለኛ ምክንያት ቅዱስ ሲኖዶሱ እንዳያውቀውና መሥራት ያለበትን ሥራ እንዳይሠራ፣ መፍትሔ እንዳይጠቁም፣ ምእመናንንም እንዳያስጠነቅቅ ሆን ብለው ትኩረቱን ወዳልሆነ አቅጣጫ በማስቀየስ አስቂኝ አስቂኝና ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት የሌላቸውን ምክንያቶች እንዲጠቅስ በማድረግ የችግሩን ትክክለኛ መንስኤ እንዳይደርስበት አድርገዋል፡፡ እነኝህ ሰዎች በዚህ መግለጫ ከየአቅጣጫው በመናፍቅነታቸው የሚሰነዘርባቸውን ውግዘት ተቃውሞና መገለል ለመከላከል ከቻሉም እንዲቆም ለማድረግ በማሰብ ውንጀላው ሐሰተኛ እንደሆነና የተወነጀሉት ጳጳሳት፣ ካህናት፣ የወንጌል አገልጋዮች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ዘማርያንና ትጉ አገልጋዮች መሆናቸውን በማድነቅ ጭምር በመግለጫው አመስግኖ የሚሰነዘርባቸውን ክስ አስተባብሎ እንዲገልጽ አድርገዋል፡፡

ይህ "የቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ ነው" የተባለው የመናፍቃኑ መግለጫ በአሁኑ ሰዓት በቤተክርስቲያን ውስጥ መናፍቃን ሃይማኖታቸውን ባስካዱቸው ተሐድሷዊያን ከሀዲያን እየታወኩች እየታመሰች መሆኗን ፈጽሞ እንደማያውቅ እንዳላየ

እንዳልሰማ ለመምሰል ከመሞከሩም በላይ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ዓይነት የክህደት የመናፍቅነት ችግር ያለበትና በጎችን የሚያውክ ተኩላ አንድም ሰው እንኳን ቢሆን እንደሌለ አድርጎ ነው መግለጫቸው እንዲገልጽ ያደረጉት፡፡

እንዲያውም እነዚህ መናፍቃን ጳጳሳት በመግለጫቸው ይድነቃቹህ ብለውም ቤተክርስቲያንን እያመሱ ምእመናንን እያስካዱ በኑፋቄ እየመረዙ ያሉትን ተሐድሶ መናፍቃን ከህዲያንን "የወንጌል አገልጋዮች፣ ዓይናማ ካህናት!" ሲሉ ጠርተዋቸዋል፡፡

መግለጫው ለማስመሰል ብቻ በአራተኛው ነጥብ ላይ "እውነተኛውን የቤተክርስቲያናችንን እምነት ሥርዓትና ትምህርት ከመጠበቅና ከማስጠበቅ ጋር ይሄንን የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርት የማይቀበሉትና የስሕተት ትምህርት ያለባቸውን ሁሉ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያወግዛል!" ቢልም መናፍቅነታቸው እየታወቀ ተወግዘው የተለዩትንና እንዲለዩ እየተጠየቀባቸው ያሉትን መናፍቃንን "ዓይናማ ካህናት፣ የወንጌል አገልጋዮች" ብለው አወድሰዋቸዋልና "እውነተኛውን የቤተክርስቲያናችንን እምነት ሥርዓትና ትምህርት" ብለው የገለጹት ቃል ለማደናገር የተጠቀሙት ቃል መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል፡፡ እነሱ "እውነተኛው የቤተክርስቲያናችን እምነት ሥርዓትና ትምህርት" የሚሉት ከህዲያኑ እየነዙት ያለው ኑፋቄ እንደሆነ ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡

እዚህ ላይ ሲኖዶስ ውስጥ ካሉትና መናፍቅ እንደሆኑ ስለሚታወቁት ሁለት ጳጳሳት የማውቀውን መናገር የሚኖርብኝ ይመስለኛ

፡፡ የጉዳዩ መቸት 1988 ዓ.ም. ጎንደር ከተማ መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ነው፡፡ ይህ ደብር ከጥንት ጀምሮ አራቱ ጉባኤያት የመጽሐፍ ትምህርት የሚሰጥበትና ማስመስከሪያ ታላቅ ደብር ነው፡፡ በወቅቱ የእነዚህ ጉባኤያት መምህር የነበሩት ታላቁ አራት ዓይና ሊቅ ሊቀሊቃውንት መንክር መኮንን ነበሩ፡፡ በጠቀስኩት ዘመን እነዚህ ዛሬ የሲኖዶስ አባል የሆኑት ሁለቱ ጳጳሳት የዚህ ጉባኤ ቤት ተማሪዎች ነበሩ፡፡

በወቅቱ ከሁለቱ አንደኛው አባ ጽጌ የደብሩ ሰንበት ት/ቤት ኃላፊ ነበሩና "በወንጌል የበሰላቹህና ለአገልግሎት ብቁ ትሆኑ ዘንድ" በሚል ሰበብ ሌላኛው አጋራቸው ትምህርቱን ይሰጠን ዘንድ ዓሥር የምንሆነውን ዲያቆናትና የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮችን ቅዳሜና እሑድ ሌሊት ሌሊት የወንጌል ጥናት ትምህርት እንዲሰጠን አግባብተውን ትምህርቱ ይሰጠን ነበር፡፡ በኋላ ሲገባኝ ትምህርቱን ሌሊት ያደረጉበት ምክንያት ሊያደርጉት ከፈለጉት ጉዳይ አኳያ ምሥጢራዊነቱን ከሌሎች የተጠበቀ እንዲሆን በማሰብና ከእኛ በኩል ግን ልጆች ናቸው ምንም አያመጡም ብለው በማሰብ ሥጋት እንደማይኖር በመተማመን ኖሯል፡፡

ይሄው ብርሃነሕይዎት የተባለ ሰው ሁለት ሦስት የሚሆን የተለያዩ ሰንበታትን ካስተማረን በኋላ በአንደኛው ቀን ያልተጠበቀ ጉዳይ ተከሰተ፡፡ ለካ የዚህ ትምህርት ዓላማ ሌላ ኖሯል መርዙን መርጨት ጀመረና የክህደት ወይም የኑፋቄ ትምህርቱን መጫን አሰቦ በትምህርቱ መሀል "ታቦት ወይም ጽላት በሐዲስ ኪዳን አገልግሎት የለውም ተሽሯል! አገልግሎቱ በአሪቱ ሥርዓት አብቅቶለታል!" አለ፡፡ እኔ ይሄንን ዓይነት የክህደት ትምህርት በፍጹም አልጠበኩም ነበር፡፡ ከዚህ እንዲቀጥል አልፈለኩም ነበርና "እንዴ! ብርሃነ ሕይዎት! ይሄ ትምህርት የቤተክርስቲያናችን ትምህርት ነው?" ስል ጠየኩት፡፡ ከምንማረው ውስጥ ሁለቱ ዲያቆናትም ከእኔ ጋር አጋር በመሆን አስከትለው "እንዴት! ምን ማለት ነው?" ብለው ጠየቁ፡፡

ይሄኔ አባ ጽጌ የተባሉት መነኩሴ እንደጠነከርንና መልስ ሳናገኝ እንደማንተው ሲገባቸው "አይ! ቤተክርስቲያን እንዲህ ብላ አታስተምርም!" አሉና "ለዛሬ ትምህርቱ እዚህ ላይ ይበቃናል" ብለው ወደ መኝታችን አሰናበቱን፡፡ ብርሃነሕይዎት ይሄንን የክህደት ትምህርት ሲሰጠን ከምንማረው ልጆች ውስጥ ከሦስታችን በስተቀር ተቃውሞውን ያነሣ አልነበረም፡፡ ለካ የተቀሩቱ ውስጥ ውስጡን መርዟቸው ኖሯል፡፡ እኛ ሦስታችንም ከዚያ ቀን በኋላ መሳተፍ አቆምን፡፡ እነሱ ግን ቀጠሉበትና ጭራሽም

ፓስተር ዳንኤል የተባለ መናፍቅ ከናዝሬት አስመጥተው ይሄንን የክህደት ትምህርት ይጠጡት ያዙ፡፡ ይሄ ነገር እየከበደ መምጣቱ አሳሰበኝና ያለውን ነገር ለደቀመዛሙርት ነገርኳቸው፡፡

ይሄንን ችግርና አደጋ ለመግታት ለእነሱ ብቻ መንገሩ በቂ ሆኖ ስላልታየኝ ለየንታ (ለሊቀ ሊቃውንት መንክር መኮንን) ለመንገር ቀጥ ብየ ወደ በአታቸው ሔድኩና ለረዳቸው እንደምፈልጋቸው እንዲነግርልኝ ተናግሬ መልስ ስጠባበቅ እንድገባ ተፈቀደልኝና ገባሁ፡፡ የሰርክ ጸሎታቸውን አድርሰው ገና መቀመጣቸው ነበር፡፡ ደኅንነቴን ጠየቁኝና ዝም አሉ፡፡ እኔም የመጣሁበትን ጉዳይ ሁሉንም ነገርኳቸው አቀርቅረው ነበር በጥሞና ያዳምጡኝ የነበሩት፡፡ ነግሬያቸው እንደጨረስኩ በድንገት ካቀረቀሩበት እንባቸው ዱብ ዱብ እያለ ሲወርድ ዓየሁ፡፡ እጅግ በጣም ደነገጥኩ፡፡ የማደርገውን አጣሁ መሬት ተከፍታ ብትውጠኝ ወደድኩ፡፡ እራሴን ያገኘሁት ሌላ ቦታ ነው፡፡ የንታን እንዴት ብየ እንደተሰናበትኳቸውና እንዴት ብየ እንደወጣሁ ምንም ትዝ የሚለኝ ነገር የለም፡፡

“ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስስ አይቀርም” ሆነና ነገሩ ሰዎቹ ከዚህ ዕኩይ ተግባራቸው ሳይመለሱ ቀሩ እንጅ ከዚያ በኋላ የንታ ለዚህ ፈተና ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ተንቀሳቅሰው ነበር፡፡ የንታ አባጽጌንና ብርሃነ ሕይዎትን ጠርተው አናግረዋቸው ነበር፡፡ እነሱ ግን እንደ አይጥ እየተሽሎከለኩ በየመኖሪያቤታቸው እየተሰባሰቡ ይሄንን የጥፋት ተግባራቸውን ቀጠሉበት፡፡ ልዑለ ቃል የተባለውንና ዛሬም አብሯቸው ያለውን መናፍቅ ከአዲስ አበባ በማስመጣት ሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሰብክ በማድረግ ደጋፊ ለማሰባሰብ ጥረት አደረጉ ጭራሽም ፓስተር ዳንኤልን ሰንበት ትምህርት ቤት ላይ እንዲሰብክ ሊያደርጉ እንደሆነ መስማታችን ከእኛ ጋራ ያላቸው ግንኙነት ይበልጥ ለመሻከሩ ምክንያት ሆነና አለመግባባቱ ወደ ጠብ ስላመራ የንታ ሰብስበውን እርቅ እንድንፈጥር ለማድረግ ጣሩ፡፡ እነሱ ግን የግብር አባታቸው ስላገበራቸው ትልቅ ሰውንና ቅዱሳንን አስጠልቷቸዋልና እዚያው ላይ የንታን የሚያህል አባት ሳይፈሩና ሳያፍሩ ለጸብ ተጋበዙ፡፡

የንታ በእነዚህ ልጆች ተግባር እጅግ በማዘንና በመደናገጥ አውጥተዋት የማያውቋትን የእጅ መስቀላቸውን አውጥተው “እኔ አወግዛለሁ! እረፉ ብያለሁ!” እያሉ ተናገሩ እርቁም ሳይሰምር ቀረ፡፡

ሰንበት ላይ ሰንበት ተማሪው እንዲሰበሰብ አደረግንና የንታ በሆነው ሁሉ እጅግ ማዘናቸውን አባ ጽጌና ብርሃነ ሕይዎት ከዚህ ተግባራቸው የማይመለሱ ከሆነ አልቅሰው ወደ እግዚአብሔር እንደሚያመለክቱባቸው አስጠነቀቁ፡፡ ሰዎቹ ግን ይሄም አላስደነገጣቸውም ነበር፡፡ ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ በመሀሉ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አሳትማ ስለማታውቅና በምእመናን እጅ የሚገኙት የተለያዩ እትሞች በሌሎች የታተሙና አስተምህሮዋን ያልጠበቁ የተቆነጻጸሉ በመሆኑ ይህ ጉዳይ በቤተክርስቲያናችን ዘወትር የሚነሣ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ አባ ጳውሎስ “ቤተክርስቲያን ያልተቆነጻጸለ የራሷን መጽሐፍ ቅዱስ ልታሳትም ነውና መጥተው እንዲያርሙ!” በሚል ምክንያት የንታን አዲስ አበባ ስለጠሯቸው የንታ አዲስ አባባ ሔዱ

ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያንም በተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲያርፉ ተደረገ፡፡ ሳምንት እንኳን ሳይቆዩ በጠና ታመሙ ተብሎ ህክምና ሲደረግላቸው ቢቆዩም ሊድኑ ግን አልቻሉም፡፡ እንደዘበት ደረስ ብለው እንደሚመለሱ ከወጡባት ሀገራቸውና ደብራቸው ሳይመለሱ አረፉ፡፡ እነ አባ ጳውሎስ ከያዙት ሰይጣናዊ ተልእኮ አኳያ መርዘው እንደገደሏቸው ታወቀ፡፡

ይህ ከባድና መራራ ኃዘን የቤተክርስቲያንና የሀገር ቢሆንም ጎንደር ግን አምርራ አለቀሰች፡፡ ከትንሽ እስከ ትልቅ ሕዝቡ በእንባ ተራጨ፡፡ እግዚአብሔር ፍርዱን እንዲሰጥ ተማጸነ፡፡ ብዙ ሳይቆዩ አባ ጽጌና ብርሃነ ሕይዎት መነኩሴ ያልነበረው ብርሃነ ሕይዎትም መነኮሰና ወዲያውኑ ወደ አሜሪካ ተጓዙ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ግለሰቦች ዛሬ አባ ጽጌ አቡነ ሰላማ ተብለው ብርሃነ ሕይዎት ደግሞ አቡነ ዮሐንስ ተብለው የሲኖዶስ አባላት በመሆን ይሄንን ሲኖዶስ ከሌሎቹ ቢጤዎቻቸው ጋር በመሆን ሥራውን እንዳይሠራና የቤተክርስቲያንን አደራ እንዳይወጣ መስመርም እንዲስት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ መናፍቃን የሲኖዶስ አባላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባላት በአስደንጋጭ ሁኔታ የቀነሰበት ምክንያት መናፍቃን ከወያኔና ወያኔ ካስቀመጣቸው ከሀዲያን ጳጳሳትና ካህናት ጋር በመቀናጀት በሚሠሩት የጥፋት ሥራና እነሱም ራሳቸው ከቤተክርስቲያን ጉያ ውስጥ ተቀምጠው የቤተክርስቲያንን እንጀራ እየበሉ ምእመናንን በማስካድ የሚሠሩት ሥራ እንደሆነ እንዳይታወቅ "የሲኖዶስ መግለጫ" ተብሎ በወጣው መግለጫ ላይ ምክንያቶች ናቸው ብለው የጠቀሷቸው አምስት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. ገዥው መንግሥት በያዘው የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኦርቶዶክሳዊያን ምእመናንን በልማት ስም ከመኖሪያ ቀያቸው ስላፈናቀላቸው ቤታቸው ፈርሶ የገቡበት የማይታወቅና ቤት ስለሌላቸው ሳይቆጠሩ የቀሩ ስለሚኖሩ፡፡

ለ. የመንግሥቱ የፖለቲካ መርሕ ኦርቶዶክሱን አማኝ ማኅበረሰብ ከመጥላቱና ካለው ረጅም ከፉ ዓላማ የተነሣ የቤተክርስቲያን ንብረት የነበሩ የታቦት ማደሪያዎች ሳይቀሩ ከቤተክርስቲያን ላይ እየተነጠቁ ለልዩልዩ ድርጅቶች ተላልፈው ስለሚሰጡና መንግሥት ካስቀመጣቸው የቤተክርስቲያን መሪዎችም ድጋፍ ሲያጣ ምእመናኑ እየተማረሩ ከአባልነት የሚወጣው ቁጥሩ ቀላል ባለመሆኑ፡፡

ሐ. ካለው የኢኮኖሚ ችግር የተነሣ በየጊዜው ወደ ዓረብ ሀገር የሚገቡ በሙቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ዓረብ ሀገር ሲገቡ የእምነት መቀየር ግዳጅ ስላለ የሚደርስባቸውና በዚሁ ስደት የተነሣ በአፍሪካና በሌላው ሀገር የተበተነውን ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ የሚቆጥረው ስለሌለና መንግሥትም የኦርቶዶክሱ ቁጥር ዝቅ ብሎ መታየቱ ደስ ስለሚለው፡፡

መ. በቤተክርስቲያኒቱ የሚካሔደው ገደብ የሌለው ዓይን ያወጣ የሙስና ሥራ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸውን ኦርቶዶክሳዊያን ልብ እየሰበረና እያደማ ከአባልነት እንዲወጡ ስለሚያደርግ፡፡

ሠ. በቤተክርስቲያኒቱ የሚከናወነው የወንጌል አገልጋዮችና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዘማርያንና ዓይናማ ካህናት በልዩ ልዩ ምክንያት በሐሰት በመወንጀል እያስመረሩ የሚያባርሩት ሕዝበ ክርስቲያኑንም ስለሚሰደድና ስለሚጠፋ ከዚህም ጋር በረሀብ መፈናቀል ከሚገጥማቸው ጋር ተጨምሮ የዚህ ሁሉ የመከራ ውጤት የቤተክርስቲያኒቱ አማኞች የመቀነሱ ምሥጢር ይህ መሆኑን ያምናል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እድገትና አንድነት እንዲጠናከር ከዚህ በላይ ለዘረዘርናቸው ችግሮች መነሻው የአሁኑ መንግሥትና እርሱ ያስቀመጠው ቤተክህነት ነው፡፡ በመሆኑም ሕዝበ ክርስቲያኑ ይህን አውቆ በልዩ ልዩ ምክንያት በሚደርስበት መከራ ተመርሮ ከቤት ከመዋልና ወደሌላ ሃይማኖት ከመግባት

ይልቅ ባለበት ቤተክርስቲያን ጸንቶ ይሄንን ቀን እግዚአብሔር እንዲያሳልፈው ሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን ተግቶ እንዲጸልይ ቅዱስ ሲኖዶሱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ነጥቦች ሆን ተብለው ምእመናንን ለማዘናጋት የተጠቀሱ ናቸው፡፡ መግለጫቸው በአንድ ቦታም እንኳን ቢሆን ቤተክርስቲያን አላግባብ አባል የሆነችበት ማኅበርም ቢሆን "የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በመባል በሚታወቀው ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አባል የሆነው ሁሉ አንዱ የሌላውን አማኝ ሰብኮም ይሁን አታሎ መውሰድ አይኖርበትን አይችልም!" የሚለውን ደንብ በመተላለፍና በምዕራባዊያን መንግሥታት ወያኔን እያስገደዱና እየደለሉ የገዛ ሕገ መንግሥቱን በሚቃረን አካሔድ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎችንና ጉዳዮችን እንዲያመቻችላቸው በማድረግ ወደ ሕዝቡና ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰርገው እየገቡ የቅድስት ቤተክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እሴት ዶግማና ቀኖና ኢጋንንታዊ በሆነ መንገድ እያጠቁ እየተቃወሙ እየሻሩ እያስተሐቀሩ ምእመናንን በማስካድ በገፍ አግዘው የወሰዱትንና እየወሰዱ ያሉትን ለዚህች ሀገር ክፉ በሚመኙትና እንድትጠፋ በሚሴሩት በምዕራባዊያኑ ተመሥርተው እንዲንቀሳቀሱ ተደርገው በሀገራችን እንደ አሸን የፈሉትን የመናፍቃን ድርጅቶችን ለዚህ ወንጀላቸው አንዲትም ቦታ ላይ ተጠያቂ ሊያደርጓቸው አልቻሉም አልፈለጉም፡፡ እንዲጋለጡ አይፈልጉምና፡፡

በመግለጫቸው የምእመናን ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ የቀነሰበት ምክንያት ብለው የጠቃቀሷቸው ምክንያቶች ተጨባጭነታቸው ምን ያህል እንደሆነ እንመርምር፡-

(ሀ) ላይ እንደገለጹት "በልማት ስም ከመኖሪያ ቀያቸው ስላፈናቀላቸው ቤታቸው ፈርሶ የገቡበት የማይታወቅና ቤት ስለሌላቸው ሳይቆጠሩ የቀሩ ስላሉ ነው" ያሉት፡፡ መናፍቃን በሚሠሩት ሥራ መንጋውን አግዘው እንደወሰዱት እንዳይታወቅና የቀረውንም አግዘው መውሰድ እስኪችሉ ድረስ እንዳይታወቅ ለማድረግ ሽፋን ለመስጠት ነው ይሄንን ያሉት፡፡ በልማት ስም የሚፈናቀለውና በመፈናቀሉም የማይቆጠር ዜጋ ካለ ወያኔ በልማት ስም እያፈናቀለው ያለው የእኛን ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ዜጋ በመሆኑ ይህ ምክንያት ብለው የጠቀሱት ነጥብ ምእመናን ለመቀነሳቸው ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ የቀነሰው የእኛ እንጅ የሌሎቹ አይደለምና፡፡

(ለ) ላይ የገለጹት "ምእመናን ወያኔ ካስቀመጣቸው መሪዎች ድጋፍ ስለሚያጡ በዚህ በመማረር" የሚለው ነጥብም በፍጹም ምክንያት ሊሆን አይችልም ባይባልም ለዚህ ኪሳራ ዋነኛውን ሚና ከተጫወቱ ነጥቦች አንዱ ግን ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡

(ሐ) ላይ የገለጹት ምክንያት "ተሰዶ የወጣው ስላልተቆጠረ" የሚለለውና በግድ እንዲሰልሙ ስለሚደረግ የሚለውም በግድ ማስለሙ ከቀረ የቆየ በመሆኑና እንዲህ ይደረግ በነበረበት ጊዜም ቢሆን ለሥራ ብለው እስላም ሳይሆኑ እስላም ነን እያሉ የሚሔዱ ዜጎች ሲመለሱ እስላም ሆነው የማይቀሩ ቁጼር እየተጠመቁ የሚቀደሱ የነበሩ በመሆኑ፣ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በስደት ያሉ ዜጎች እዚህ ባሉ ቤተሰቦቻቸው የሚቆጠሩበት አሠራር ያለ በመሆኑ ኢትዮጵያ ክርስቲያኑም እስላሙም ምኑም ተደምሮ ባጠቃላይ ያላት ስደተኛና ከሀገር ወጥቶ የሚኖረው ሕዝብ ሦስት ሚሊዮን (አእላፋት) ብቻ በመሆኑና ከዚህ ቁጥር ግማሹ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተከታይ ነው ብንልና ሆን ተብሎ እንዳይቆጠር ተደርጓል ብንል እንኳ ቤተክርስቲያን ከተነጠቀችው መንጋ አንጻር ይሄ ቁጥር ሲታይ ኢምንቱን እንኳን የሚያህል ባለመሆኑ ይሄም ምክንያት እንደዋነኛ ነጥብ ሊጠቀስ የሚችል አይደለም፡፡

(መ) ላይ የጠቀሱት "ምእመናን በሙስና ልባቸው እየደማ ከአባልነት እንዲወጡ ስለሚያደርጋቸው" ያሉትም እንደሌሎቹ ነጥቦች ሁሉ በፍጹም ምክንያት ሊሆን አይችልም ባይባልም ከዋነኛ ምክንያቶች አንዱ እንዳልሆነ ግን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በመጨረሻው ነጥባቸው (ሠ) ላይ የገለጡት ግን ይሄንን መግለጫ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም ያወጡ ሰዎችን ማንነት በትክክል ያጋለጠ ነጥብ ነው "በቤተክርስቲያኒቱ የሚከናወነው የወንጌል አገልጋዮችና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዘማርያንና ዓይናማ ካህናት በልዩ ልዩ ምክንያት በሐሰት በመወንጀል እያስመረሩ የሚያባርሩት ሕዝበ ክርስቲያኑንም ስለሚሰደድና ስለሚጠፋ" ያሉት ይታያቹህ ምእመናንን እያስኮበለሉ ወደ መናፍቃኑ እንዲጋዙ እያደረጉ ያሉትን ከሀዲያን ተኩሎችን "የወንጌል አገልጋዮችና ዓይናማ ካህናት" ብለው ከማድነቃቸውም በላይ ተኩላዊ ተግባራቸው ተነቅቶባቸው ምእመታንና ታማኝ ካህናት ተባብረው እንዲገለሉ በማድረጋቸው እነሱ ስለተባረሩ ነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አማኞች ቁጥር የቀነሰው ብለው አረፉት፡፡ መገለል እንደሌለባቸውም አበክረው ይናገራሉ ያስጠነቅቃሉ፡፡

ሲጀመር እዚህ ያሉት የወያኔ ጳጳሳት እነ አባ ማትያስም ኑፋቄ ያለባቸው ጳጳሳት ያሉበት በመሆኑና እነ አባ ማትያስ የሙሉ ጊዜ ሥራቸው የወያኔን ደኅንነትና ህልውና ተግቶና ነቅቶ መጠበቅ እንጅ ሐዋርያዊ ተልእኮን መወጣት ቤተክርስቲያንን መጠበቅ ባለመሆኑ ለወያኔ አደጋ እስካልሆኑና እስካልተቃወሙ ጊዜ ድረስ የመናፍቃኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ መፈንጨትና በጎችን ማስኮብለል የሚያስደስታቸው እንጅ የሚያሳስባቸው ጉዳይ አይደለምና ማንንም ሰው መናፍቅ ወይም ተሐድሶ በመሆኑ አባረው አያውቁም፡፡

ሰሞኑን ግን ተፈጻሚነቱ ባይታወቅም የምእመናን ጫናና ጥያቄ እጅግ እያየለ በመምጣቱ ተሐድሶ መሆናቸው የሚታወቁ ቡድኖችን በቤተክርስቲያን ስም የራሳቸውን አገልግሎት እንዳይሰጡ እንዳይሰብኩ ውሳኔ አሳልፈዋል፡፡ ከዚህ ቀደምም እርምጃ የተወሰደባቸው መናፍቃን እርምጃው የተወሰደባቸው እነ አባ ጳውሎስ የቤተክርስቲያን ጠባቂነቱ ተሰምቷቸው እርምጃውን የወሰዱ ሆነው ሳይሆን እንደዚሁ የምእመናንና የምሁራን ጫናና ጥያቄ እጅግ አይሎ ለራሳቸውም የሚያሠጋበት ደረጃ በመድረሱ ነው እርምጃው የተወሰደው እንጂ እነ አባ ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ባላቸው ቀናኢነት ይሄንን እርምጃ እንዳልወሰዱና እነ አባ ጳውሎስም ሆኑ እነ አባ ማትያስ ኑፋቄ ያለባቸውን ካህናትን ዘማርያንን ሰባክያንን አማሳኞቹን እንደሚያተጉ እነደሚያበረታቱ እንደሚደግፉ ወደ ኋላ በምገልጸው መረጃ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ባጠቃላይ የጠቀሷቸው አምስት ምክንያቶች ሕዝበ ክርስቲያኑ ትክክለኛውን ምክንያት አውቆ አስፈላጊውን እርምጃ እንዳይወስድ የሚጋርዱ የሚከልሉ የሚያዘናጉ ናቸው፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሰዎች የሄንን ያህል ናቸው፡፡ ማንነት አስተሳሰባቸውም ይሄ ነው፡፡ አሁን ታዲያ እነዚህ ናቸው የመንጋው እረኞች? እነዚህ ናቸው የቤተክርስቲያን ጠባቂዎች? ይሄ መግለጫስ መናፍቃኑ ሲኖዶስን ሳይቀር በመውረር ምን ያህል ቤተክርስቲያንን እስከመቆጣጠር እንደደረሱ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ አይደለም?

ቅዱስ ፓትርያርኩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከበዋቸው ያሉትን መናፍቃን ጉድ የማያውቁ እንዳይመስላቹህ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ይሄ ችግር ፈጥጦ የሚታይ ግልጽ ጉዳይ ቢሆንምና ቅዱስ አባታችን እየተቀበሉት ያለው መከራ እየፈጸሙት ያለው ተጋድሎ ለብቃት ደረጃ ያበቃቸው ቢሆንም ቅሉ የመነፈቁ ጳጳሳትንና ካህናትን ለይተው እንዲያውቁ ብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አያስፈልጋቸውም ባይጠበቅባቸውም ነበር፡፡ "ካወቁ ታዲያ ለምን በዝምታ ይመለከቱታል?" የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል፡፡ መልሱ ግን እንዲህ እንደጥያቄው ቀላል አይደለም ብዙ የቸገረ ነገር አለ፡፡

ቅዱስ አባታችን ከበዋቸው ያሉት መናፍቃን ጳጳሳት ከአቅማቸው በላይ ሆነውባቸው እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ ስላልሆኑ፣ አብረዋቸው ያሉት ደኅናዎቹ ጳጳሳትም እንደሳቸው ሁሉ በመናፍቃኑ ጳጳሳት ስለሚዋከቡና አቅመ ቢስ ስላደረጓቸው፣ እንደ ቅዱሳን አባቶቻቸው ሁሉ እንዲህ ዓይነት የቸገረ ነገር ሲገጥም "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር" ብለው እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠራ ለእግዚአብሔር ፋንታን ስለሰጡ ነው ምንም እንደማያውቅ ሰው በዝምታ የሚመለከቱ መስለው የሚታዩት፡፡

ይህ የገጠማቸው ፈተና ከአቅማቸው በላይ በመሆኑና ለቤተክርስቲያንም ለሀገርም ለታሪክም ለማንነትም የከፋ አደጋ ያለው መሆኑን ጠንቅቀው ስላወቁም ነው እግዚአብሔር መፍትሔ እንዲሰጥ ከስደት ዘመናቸው የሚበዛውን ያለ እረፍት በሱባኤያት በማሳለፍ በእርጅናቸው ላይ እራሳቸውን እንደዚህ ዓይነት የሱባኤ መከራ በመቀበል በመጥመዳቸው ጤናቸው በየጊዜው ለአደጋ እየተዳረገ ለህክምና የሚወሰዱ የሆኑት፡፡ ሱባኤ እንዲያቆሙ ምግብ በአግባቡ እንዲመገቡ ሀኪሞች አበክረው ቢያሳስቡም እሳቸው ግን በፍጹም ሱባኤ ሊተው አልቻሉም፡፡

ሱባኤ በጣም ከባድ ነው እንኳንና ይሄንን ያህል ዘመን ያንድ ጊዜና የሁለት ጊዜው እንኳን ሰውነትን እንዴት አድርጎ እንደሚጎዳ የመናንያንን ሕይወትና ተጋድሎ በቅርበት የሚያይ ያውቀዋል፡፡ እንግዲህ ምን እላለሁ? እንዲህ ሆነው የሚማጸኑትና የተማመኑበት አምላካቸው መድኃኔዓለም ክርስቶስ ጩኸታቸውን ተማጽኗቸውን ልመናቸውን ሰምቶ ቅድስት ቤተክርስቲያንን ከአጋንንት አፍ ይታደጋታ!!!

ቅዱስ አባታችን ከመጀመሪያው የእነኝህ የወረሯቸውን መናፍቃን አደገኛነትና በቤተክርስቲያን በሀገር ላይ የጋረጡትን አደጋ እጅግ ከመፍራታቸው የተነሣ ከአዲስ አበባዎቹ የወያኔ ጳጳሳት ቡድን ጋር የእርቅ ድርድር ይደረግ በነበረበት ጊዜ ሕገ

ቤተክርስቲያን ባይፈቅድላቸውም እነ አባ ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ታማኝ መሆናቸውን በመሐላ ሊያረጋግጡላቸው ከቻሉና ቃል የሚገቡላቸው ከሆነ ፓትርክናቸውን አሳልፈው በመስጠት በበኣት ለመወሰን እስከመሻት ድረስ እንዲያስቡ አድርጓቸው ነበር። ከበዋቸው ያሉት መናፍቃኑ ይሄንን የቅዱስ አባታችንን ሐሳብ ስለሚያውቁ ከማንም ጋር እንዳይገናኙ አድርገዋቸዋል። ሌላው ቀርቶ በዘመዶቻቸው እንኳን እንዲጎበኙ እንዲጠየቁ በፍጹም አይፈቅዱላቸውም።

በዚህ አጋጣሚ እዚያው ሀገር ላላቹህት ካህናትና ምእመናን የተዋሕዶ ልጆች በሙሉ አጥብቄ ማሳሰብ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር ቤተክርስቲያን በዘመኗ ዓይታው በማታውቀው ከባድና እጅግ አሳሳቢ ፈተና ላይ ነው ያለችው። እዚህ ሀገር ቤት ያለነው ካህናትና ምእመናን የወያኔ ጳጳሳትና ካህናት ቤተክርስቲያንን መጫዎቻ መቀለጃ ሲያደርጓት በቆመችበት ደርቃ እንድትከስም ደም ስሮቿን ሲቆርጡና በርካታ አጋንንታዊ ተልእኳቸውን ሲፈጽሙባት ዓይተን መታገስ ባለመቻላችን ስንቃወም በጠባቂያቸውና አሥሪያቸው ወያኔ አፈሙዝ እየተቀጠቀጥን የመከራ ዓይነት እየዘነበብን እንድናርፍ ስለተደረግን ይሄው እንደምታዩን በዝምታ እየተመለከትን እንገኛለን።

እናንተ እዚያ በነጻነት ሀገር ያላቹህትና ለሙብታቹህ ተጋደላቹህ፣ ቤተክርስቲያናቹህን ጠበቃቹህ፣ ለቤተክርስቲያናቹህ ተቆረቆራቹህ፣ ተሟገታቹህ ብሎ አፈሙዝ የሚያዞርባቹህና በእኛ ላይ እንደሆነው የመከራ ዓይነቶችን የሚያዘንብባቹህ ኃይል ሳይኖር በቤተክርስቲያን ላይ ይሄንን ያህል ጉዳት ያደረሱብንን የመጥፋት አደጋን በቤተክርስቲያናችን ላይ የጋረጡትን መናፍቃን ጳጳሳትና ካህናትን መቃወም ማስወገድ ማባረር እየቻላቹህ ቤተክርስቲያንን ያስበላቹህት ምን ነክቷቹህ ነው? ምእመናኑን አጠቃለው እስኪበክሉና እስኪረከቡ ነው ወይ የምትጠብቁት? መናፍቃኑ በቤተክርስቲያን ላይ እንዲህ ሲበረቱባት ሲያጠቋት ሲያጠፏት በዝምታ በማየታቹህ በጌታ ዘንድ ከእነሱ እኩል ተጠያቂ የማትሆኑ ይመስላቹህል? ጳጳሳት ለሃይማኖት የመቆርቆር ቤተክርስቲያንን የመጠበቅ ላቅ ያለ አደራና ኃላፊነት ቢኖራቸውም ቤተክርስቲያንን ከጥፋት የመጠበቅ ግዴታ ግን የአንድ ጳጳስና የአንድ ተራ ምእመን ግዴታ አንድ እንደሆነ አታውቁምን?

እናም እባካቹህ በእነዚህ መናፍቃን ላይ ቆርጣቹህ ተጠናክራቹህ በመዝመት ቅዱስ አባታችንንና ሌሎቹንም ደጎና የሆኑትን ጳጳሳት ማለትም ሲኖዶሱን ነጻ አውጥታቱህ የመናፍቃኑን እጅ በመቁረጥ ቤተክርስቲያንን ከጥፋት ታደጓት??? አሁኑኑ ፈጥነን ያልተነሣን እንደሆነ ይሄንን አደጋ መቀልበስ በፍጹም እንደማንችል ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል።

ትክክለኛውና እውነተኛው ምእመናንን በአስደንጋጭ ሁኔታ እንዲቀንሱ ያደረገውና በአጭር ጊዜ ውስጥም ቤተክርስቲያን አንድም እንኳ ምእመን እንዳይኖራት አድርጎ እርቃኗን ሊያስቀር የሚችለው ዋነኛውና ብቸኛው ምክንያት የሚከተለው ነው፡-

ደርግ ወድቆ የወያኔን መተካት ተከትሎ ወያኔ "ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛውን ቁጥር የያዘችውንና ጠንካራ መዋቅር ያላትን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በቁጥጥሬ ስር ሳላደርግ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ተቆጣጠርኩ ማለት ከቶውንም አልችልም! አሥተዳደሬም የተረጋጋ ሊሆን አይችልም!" የሚል እምነት በመያዙ ቤተክርስቲያን የምትተዳደርባቸውን ቀኖናዎቿንና ሥርዓቷን በማፈራረስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን አሳዶ ከሀገር በማስወጣት የራሱን ሰው አባ ጳውሎስንንና ወያኔ በትግል ላይ እያለ አስቀድሞ ለዚሁ አገልግሎቱ ሲል መጠነኛ የቤተክርስቲያን ትምህርት እንዲያገኙ አድርጎ ያዘጋጃቸውን ታጋዮቹን በካህን ስም አስገብቶ (ብዙዎቹ ዛሬ ላይ ጳጳሳት ሆነዋል) ቤተክርስቲያኗን መቶ በመቶ በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ዶግማ ቀኖናዋን ከመቆነጻጸል ጀምሮ እስከ ቅርስ ንብረት ገንዘቧ ድረስ ያሻውን የፈለገውን በማድረግ ዝርፊያና ውድመት ሲፈጽምባት ቆይቷል እየፈጸመባትም ይገኛል።

ይህች ቤተክርስቲያን በወያኔ ከደረሰባት ኪሳራና ጉዳት ከሁሉም በላይ የሚቆጨውና የሚያገበግበው ደግሞ ወያኔ እሱን ለዚህ ካበቁት ምዕራባዊያን በተሰጠው ተልእኮ ምክንያት ከመናፍቃን ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ በመሥራትና የገዛ ሕገመንግሥቱን በመጻረር ለመናፍቃኑ በሚያደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ የቤተክርስቲያኗ ምእመናን እንዳለ ተወስዶ የምእመናኖቿ ቁጥር ከኢትዮጵያ ሕዝብ 55 በመቶ ከነበረበት የቅርብ ጊዜው አኃዝ በዘመነ ወያኔ በተደረጉ ሁለት ቆጠራዎች እየቀነሰ መናፍቃኑ ደግሞ በወያኔና አባ ጳውሎስን ጨምሮ እሱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ባስቀመጣቸው ከሀዲያን በሚደረግላቸው ድጋፍ በሚፈጥርላቸው ሕገ ወጥ የሆነ ምቹ ሁኔታዎች በመታገዝ በእጥፍ በእጥፉ እየጨመሩ መጥተው ምእመናኖቿን አግዘው በመውሰዳቸው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባላት አሽቆልቁሎ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ዘንድሮ ይደረጋል በተባለው የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ከ 15 እስከ 20 በመቶ ባለው ቁጥር መሀከል እንደሚሆን ተገምቷል፡፡

እጅግ የሚያስደነግጠውና የሚያሳዝነው ጉዳይ ይሄ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ቆጠራ በየ ዓሥር ዓመቱ እንደመደረጉ ሁሉ ወደ ፊት ከ 10 ዓመታት በኋላ ማለትም 2018 ዓ.ም. በሚደረግበት ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አንድም አባል እንኳን ሳይኖራት ነበረች ተብሎ የሚነገር መሆኑ ነው፡፡

ይህ የመናፍቃንና የወያኔ የተቀናጀ ጥረት ስኬት እንዴት ሊገኝ ቻለ? ብለን የጠየቅን እንደሆነ  ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በገዛ ሕገ መንግሥቱ ላይ “ለአምልኮ ከተፈቀደ ቦታ በስተቀረ በመንገድ፣ መጓጓዣ በመጠበቂያ (ፌርማታ)፣ በሥራ ቦታዎች፣ በመዝናኛ ቦታዎች ወዘተረፈ. መስበክ የተከለከለ ነው!” ብሎ ቢደነግግም መናፍቃኑ በእነዚህ ቦታዎች ብቻ ሳይሆን ቤት ለቤት ሁሉ ሳይቀር እያንኳኩ የክህደት ስብከታቸውን እየሰበኩ በጎቻችንን ሲነጥቁ ይህ አድራጎት የተከለከለ በመሆኑ ከዚህ አድራጎታቸው እንዲታቀቡ ማድረግ ሲገባው ያለ አንዳች ሥጋትና እቀባ የክህደት ስብከታቸውን በምእመናን ላይ እንዲዘሩና እንዲያሰናክሉ በማድረጉ፣ በመላ የሀገሪቱ ቦታዎች የቀበሌ አዳራሾችንና “የእርሻ ሰብል” ይባል የነበረውን ድርጅት የእህል መጋዘኖችን ሌሎች የመንግሥት ንብረቶች የሆኑ አዳራሾችን ሁሉ ሕገ ወጥ በሆነና አግባብነት በሌለው አሠራር ለመናፍቃኑ መስበኪያ መደንከሪያ ማበጀ እየሰጠ ለዚህ የጥፋት ተልእኳቸው የማያሰልስ ድጋፉን በማድረጉ፣ አሁንም በሕገ መንግሥቱ የተከለከለውን ማለትም ማንኛውም ድርጅት “ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን ወዘተረፈ. በመክፈት፤ እርዳታ በመለገስ ሃይማኖትን ማስቀየር የተከለከለ ነው!” ቢልም ወያኔ ግን በዚህ ረገድም ለመናፍቃኑ የማያሰልስ ድጋፉን እየሰጠና ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረላቸው ተጠያቂ ሳያደርጋቸው ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየከፈቱ ለተቸገሩ ዜጎች ወርኃዊ እርዳታ በመለገስና ወደ እነሱ እንዲገቡ ሃይማትን እንዲክዱ እያደረጉ እንዲስፋፉ በማድረጉ፣ በአንጻሩ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ግን በሾማቸው ከሀዲያን አሳስሮ በማስቀመጥ፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን እያሳደደ በማጥፋት፣ ትክክለኛና የቤተክርስቲያን የመንጋው ጉዳይ የሚገዳቸውን አባቶችን መምህራንን ካህናትን በየትኛውም ቤተክርስቲያን ላይ ማገልገል እንዳይችሉ በማድረግና በማባረር በማሳደድ በማጥፋት፣ እራሳቸው መናፍቃን የእኛን ቤተክርስቲያን መድረኮችና የቤተክርስቲያንን ንብረቶች ሁሉ እየተጠቀሙ እንዲስፋፉ በመደረጉ (አባ

ጳውሎስ ለመናፍቃኑ የተለያየ ዓይነት ድጋፍ ማድረጋቸው በመረጋገጡ ለመጨረሻ ጊዜ በተሳተፉበት የጳጳሳት ስብሰባ ላይ እነሱ ሲኖዶስ ይሉታል “ሃይማትዎ ምንድን ነው?” ተብለው ተጠይቀው በማግስቱ ለሚቀጥለው ስብሰባ መልስ እንዲያቀርቡ ተቀጥሮ ጳጳሳቱ ቢጠብቁም አባ ጳውሎስ ግን ሳይገኙ መቅረታቸው ያታወሳል) እነዚህ እነዚህን በመሳሰሉ መሰናክልና ፈተናዎች ቤተክርስቲያን እንድትሽመደመድ በመደረጉና እየተደረገም ስላለ ነው መንጋዋ ተጠርጎ የተወሰደው፡፡ ለዚህም ነው አቦይ ስብሐት ነጋ “የኦርቶዶክስን አከርካሪ ሰብረናል እንዳያንሰራራ አድርገን አዳክመነዋል!” ሲሉ የተናገሩት፡፡

መድኃኔዓለም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ከአጋንንት አፍ ታድጎ ሰላሟን ይመልስ ህልውናዋን ያረጋግጥ ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

ethiopanorama